## ክህደትና ህሊና ፤ ኢህዴን/ብአዴንና የበለሳ ህዝብ ትዝብት

በቅርቡ ጋዜጠኞችን አስከትለዉ የብአዴን ፓርቲ ቱባ ቱባ ጥቂት መሪዎች ወደ ጎንደር በለሳ አካባቢ ተጉዘዉ እንደነበር አስነብበዉናል። የጉዞዉ አላማ ምን አልባት "የሚወዳቸዉንና የሚወዱትን" የበለሳን ህዝብ ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ የሚዉል ዘገባ ሊሰሩበት አስበዉ ሳይሆን አይቀርም። የተጓዙበት ልዩ ስፍራ ደግሞ አርባ ጸጓር የተባለች በተከዜ ወንዝ አጠገብ የምትገኝ ለዋግና ለበለሳ ኗሪዎች መናህሪያ የሆነች፤ በጸረ ደርግ ትግሉ ወቅት ዋና የድጋፍ መሰረት የሆነች ወረዳ ናት።

ጋዜጠኛ ፋኑኤል ክንፉ እንደዘገበዉ የአርባ ጸጓር አርሶ አደር ከኢህአሰ/ኢህአፓ ጎን ተሰልፎ፤ ፓርቲዉንና ሰራዊቱን ደግፎ ብዙ ትግልና መስዋእትነትን የከፈለ አካባቢ ነዉ። ባንድ በኩል በደርግ፤ በሌላ በኩል በወያኔ ኢህአደግ በደረሰበት ድርብ ግፊት በኢህአፓ ዉስጥ በተፈጠረዉ ቀውስ፤ ራሱን ኢህዴን ብሎ የሰየመዉ (ራሱ ነዉ ወይስ ወያኔ "ብአዴን" ብሎ ካጠመቀዉ የሁለተኛ ጊዜ ስም በፊት ያወጣለት የመጀመሪያ ስሙ ነዉ?) ቡድን እዚሁ አካባቢ ሲንቀሳቀስም፤ ይህዉ አርሶ አደር ህዝብ እንደ ኢህአፓዉ ጊዜ የእዉነት ታጋይ አግኝቻለሁ ብሎ በኢህ አፓ ጊዜ ከከፈለዉ ያላነሰ መስዋእትነት ከፍሎ ነበር። በድርቅ ተደጋግሞ ከመመታቱ በፊት በነበረዉ ወርቃማ ዘመን ቤቱ ያፈራዉን ወተት፤ እንጀራና ወጥና ጠላ ለኢህዴን ተለጣፊዎች በታማኝነትና በሃገር ፍቅር ያቀረበና የቀለበ አካባቢ ነበር።

ታዲያ ከ **25** አመታት በኋላ የ ኢህ አዴን/ብአዴን ሹመኞች በምቾትና በሙስና ታዉረዉ የረሱትን ህዝብ የግፍ ግፍ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንደሚባለዉ፤ ለወሬ ፍጆታ ብቻ በሚመስል ሊፈልጉት ሲሄዱ የጠበቁት ሳይሆን ያልጠበቁትን የሃፍረት ማቅ ያከናነባቸዉ ክስተት አጋጥሟቸዋል። እንደ ጋዜጠኛዉ አባባል፤ በአርሶ አደሩ የተነሱት ጥያቄዎች እንኳን የዶኩመንታሪ ፍጆታ ወሬ ሊሆኑ፤ የአጃቢ ጋዜጠኞችን ልብ የሰበሩና ያስለቀሱ ነበሩ። ጋዜጠኛዉ በራሱ ቃላት ስለ አርሶ አደሮች እንዲህ ይላል " አንደበታቸዉ የሚፋጅ እዉነቶችን ቶሎ ቶሎ ይተፋል፤ ገጽታቸዉ ቁጭት፤ እልህ መገፋትና መካድን ያሳያል። ተስፋቸዉ ሙሉ በሙሉ የተሟጠጠ መሆኑን ለመረዳት የሮኬት ሳይንስ አያስፈልግም"።

## አርባ ጸጓር ወረዳ ምን ደርሶበት ይሆን ይህ ሁሉ ምሬት?

አርሶ አደሮቹ ለቱባ ሹማምንቱ ያሰሙት ሮሮና ጋዜጠኞቹ የከተቡት፤ አካባቢዉ ተከዜ አጠገብ ተቀምጦ ንጹህ የመጠጥ ወሃ እንኳን እንደማያገኝ፤ በዚህ ምክንያት የሚጠጡት ወሃ የከብት ሽንት እንደሆነ፤ ሩቅ ሄደዉ የሚያመጡት ወሃ መራራና ቆሻሻ መሆኑን፤ በታይፎይድ በሽታ ትልቁም ትንሹም በቆሻሻ ወሃ ምክንያት እንደተበከሉ ብሶታቸዉን ገልጸዋል። እስካሁን ድረስ ዳዋዉንም ገደሉንም እየጣሱ ወሃ ያመጡ እንደነበረ፤ አሁን ግን በወሃ እጦት ምክንያት የቀበሌዉ ኗሪ ሊበታተን እንደሆነ - ገሚሱ መና ወደ ተባለ ወንዝ አካባቢ፤ ገሚሱ ደግሞ ወደተከዜ እንደሚሄድ በብርቱ ሃዘን የሚሰማ ጆሮ ያገኙ መስሏቸዉ አስታዉሰዋል።

መብራትን አስመልክቶ ደግሞ ከዘመናዊ መብራት መራቃቸዉን ተናግረዋል። ጽድቁ ቀርቶ በወጉ በኮነነኝ የሚያሰኝ አይነት ነዉ። በጤና በኩልስ? ህክምና ለማግኘት እስከ **60** ኪ.ሜ. አቆራርጠዉ እንደሚሄዱ፤ እንዲያዉም ሹማምንቱ ከመምጣታቸዉ አንድ ቀን በፊት አንዲት የምታምር ልጅ እባብ ነድፏት እንደሞተችና አንጠልጥለዉ ይዘዉ ወደ ጤና ጣቢያ እስኪወስዷት ጊዜ እንዳልሰጣቸዉ በሃዘን ተናግረዋል። ሌላዉ ቢቀር እንኳን ለእባብ የምትከላከል ጤና ጣቢያ ስሩልን ብለዉ ተማጽነዋል።

በአጠቃላይ አርባ ጸጓር ዉስጥ ያለችዉ "ልማት" አንዲት ትምህርት ቤት ናት። ለዚያዉም መንግስትም ሆነ ሌላ በጎ አድራጊ ያልረዳት፤ በራሳቸዉ በአርሶ አደሮች ጥረት የተሰራች ናት።

ጋዜጠኞቹ ራሳቸዉ በአርሶ አደሮቹ ስቃይና ምሬት እጅግ ግራ እንደተጋቡ ዘገባቸዉ ያሳብቃል። "ልብ የሚነካ፤ ግራ የሚገባ ስሜት ፈጠረ" ብለዉ ነዉ የገለጹት። እንዴት ግራ አይገባቸዉ?

አንደኛዋ ሴትዮ ምስላቸዉ ዘገባዉ ላይ የሰፈረ የታጋይ ቤተሰብ ነበሩ። ከቤተሰቡ መካከል መሃባዉ ዳዊትና ደሴ ዳዊት በትግል ተሰዉተዋል። "ደርግን ጥለን የዴሞክራሲ፤የሰላምና አንድ አይነት ኑሮ እንኖራለን ብለን ከኢህዴን ጋር መክረን ነበር። የተማርነዉም ያልተማርነዉም አንድ ላይ ተጠርንፈን እንኖራለን ተብሎ ነበር፤ ያ ሁሉ ያወጋነዉ የት ሄደ? አብረነን የበላነዉ የጠጣነዉ የት ሄደ? እንዴት ችግራችንን የሚያዉቁን አይነግሩልንም? አይፈቱልንም? አዲሶችስ ስለማያዉቁን ችላ ብለዉን ይሆናል፤ ዛሬ ነጻነት ሲገኝ እንዴት ረሱን? እዚህ ከኛ ጋር በትግሉ የነበሩ ሰዎች እንዴት ችግሩን ረሱት? ርሃብ ጥማቱን እንግልቱን ያዉቁት የለም እንዴ? ያን ሁሉ መከራ ቆሎ ተሸክመን፤ጥይት ተሸክመን፤ የታጋይ ልጆች በረንዳ አዳሪና በሽርሙጥና አዳሪ

ሲሆኑ፤ የሚች ልጆች ወድቀዉ ሲቀሩ፤ ትንሽ ገንዘብ ያላቸዉ ወደላይ ሲነሱ እኛ ወደቅን " እያሉ ብዥታቸዉን ከእንባ ጋር ያፈሱት

## ቱባ ሹማምንት በመልሳቸዉ ዳግም ክህደታቸዉ!

የኢህዴን/ብአዴን ሹማምንት ከተጨባጭ ሁኔታዉ ዉጭ መሆናቸዉንና እንዲያዉ በራሳቸዉ የምቾት ኑሮ አይናቸዉ እንደታወረ ለአርሶ አደሮቹ ከሰጡት መልስ ግልጽ ይሆናል።

አንደኛዉ ቀልደኛ ሹም ይህን ሁሉ አስዛኝና አሳፋሪ የድህነት ታሪክ ከሰማ በኋላ ስለወሃዉ ችግር " አካባቢዉ የከርሰምድር ወሃ የለዉም (በየትኛዉ ጥናት ተመስርቶ እንደሆነ አንባቢ ይታዘብ)። ወሃ ማግኘት የሚቻለዉ ከዚህ በ **30** ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ከሚገኘዉ መና ወንዝ አልያም ከዚህ **60** ኪ.ሜ. ርቀት ከሚገኘዉ ተከዜ ወንዝ ወሃ በመጥለፍ ነዉ። ይህን ለማድረግ በጣም አስቸጋሪ ነዉ!!( አስቸጋሪ? ? አገሪቱን ግድብ በግድብ አድርጊያለሁ እያለ የሚፎክር መንግስት፤ ተከዜ ራሱ ላይ ግድብ ሰርቶ ኤለክትሪክ ተጠቃሚ ለሆኑት በረከት የሚሰጥ መንግስት ለ አርባ ጸጓር ወረዳ አርሶ አደር ወሃ ለማቅረብ አስቸጋሪ ነዉ ይላል?)

ይህ ቱባ ሹም በዚህ አላበቃም። ቀጠለ..."ለዚህ (ተከዜን ለመጥለፍ) የሚያስፈልገዉ የበጀት መጠን ወገብ የሚሰብር ነዉ!!" እስከ **12** ቢሊየን ብር የአገሪቱን ሃብት በምዝበራ የሚሰርቅ መንግስትና ኤፈርት በተባለ ባለ ቢሊዮን ብር የግል የወያኔ ሃብት አካል የሆነ ሹም "ወገብ ስለሚሰብር" በጀት ለአርሶ አደሮች ይደሰኩራል። በመዝጊያዉ ደግሞ የለበጣ ቃል ኪዳን "አሁን ላይ ግን አካባቢዉ ድርቅ ያጠቃዉ በመሆኑ መንግስት ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ "በልዩ ሁኔታ" እያየዉ ነዉ"። ወያኔ ድርቅ ላጠቃቸዉ አካባቢዎች ልዩ ትኩረት ይሰጣል ካለበት ስልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ የበጀት ፈሰስ ላደረገላቸዉ አካባቢዎች ርዳታ አድርጎላቸዋል። አርባ ጸጓር ግን መመዘኛዉን ከሚሟላት በላይ ቢሆንም ምንም ርዳታ አለማግኘቱ ከአስተዛዛቢ በላይ ነዉ።

ሌላኛዉ ባልተኛ ሹምስ ምን መልስ ሰጠ? "በርግጥ በዉስጣቸዉ ብሶት ስላለ ተናገሩት እንጂ ማናችንም የታገልነዉ ለግላችን አይደለም!!!?" "**Really?**"ይላል ፈረንጅ በስላቅ ሲናገር። ቱባ ሹማምንቱ ወፍራም ደመወዛቸዉን እየዛቁ፤ በሚያምር ቪላ እየኖሩ፤ የንጹህ ወሃ፤ መብራትና ምግብ ሃሳብ ሳይኖራቸዉ አንዳንዴም በሙስና የህዝብ ንብረት እየዘረፉ "ለግላችን አይደለም የታገልነዉ" አርፋችሁ ተቀመጡ፤ ወይም ይገባናል አትበሉ የሚል ወቀሳ በምቾት ከታወረ ሹም ብቻ የሚመነጭ አሳዛኝ አስተያየት ነዉ።

ሹሙ በዚህም አላበቃም። "ህብረተሰቡም መታገል አለበት። እንዲሁም መንግስት። ተስፋ አትቁረጡ"። የተወለድንበትን መንደር ትተን በወሃ ጥምና በችግር ምክንያት ልንሰደድ ነዉ፤ ጤና ካለ የሚበላ ካለበት ስደዱን፤ ሁሉም አገራችን ነዉ ሄደን እንኖራለን" እያሉ በመጨረሻዋ ደቂቃ ላይ በቋፍ ላይ ያሉ አርሶ አደሮችን "ህብረተሰቡም መታገል አለበት" ማለት ምን የሚሉት ቀልድ ነዉ?

አንደኛዉ ሹም የህበረተሰቡን ያለፈ የትግል ታሪክ በምስክርነት ማስቀመጡ ለዛሬዉ አልረዳም እንጂ ጥሩ ነዉ። "የነቃ ህብረተሰብ ነዉ፤ በህብረተሰቡ ማርክዚዝምን ከነአስተምህሮቱ ታገኛላችሁ።እንዲሁም ቁስ አካልን ጨምሮ። ሴቶቹ በጣም ሃይለኞች ናቸዉ። ከኢህ አፓ ጀምሮ ለነጻነታቸዉ የሚታገሉ ነበሩ"።

እነዚህ ሹማምንት ልባቸዉን ክህደት ይሁን ምቾት ወይም ሌላ ደፈነዉ እንጂ እንኳን በትግልና በችግር ጊዜ የሚያዉቁትን ህብረተሰብ፤ ሌላዉንም የኢትዮጵያ ክፍል እንዲህ አይነት ጥያቄዎች ሲነሱ በሃላፊነት መዉሰድ የነበረባቸዉ ርምጃዎች መኖር ነበረባቸዉ። ቢቻል ሁኔታዉ ተባብሶ እዚህ እስኪደርስ መቆየት አልነበረበትም። ከሆነ በኋላ ደግሞ የመንግስት ሹማምንት ስለሆኑ ተቆጣጣሪያቸዉን ወያኔን አፋጥጠዉም ሆነ አስረድተዉና ለምነዉ በጀት የሚፈቀድበትን መንገድ ያለመታከት መፈለግ ነበረባቸዉ።

እስከዚያ ድረስ ግን የአርሶ አደሮቹን ልብ ዳግም የሚያደማ መልስ ከመስጠት " መንግስት በአፋጣኝ መልስ እንዲሰጣችሁ እንሞክራለን፤ እስከዚያዉ ግን በአመት ያንድ ወር ደሞዛችንን ከእያንዳንዳችን በመለገስ ለአርባ ጸጓር ልማት እንዲዉል ወስነናል" ማለት ማንን ይገድላል? ለዚያዉም በትግሉ ወቅት አጓትና ወተት ላጠጣ፤ እንጀራ ላበላ አርሶ አደር? ነጻ ፍርድ ቤቶች ቢኖሩ እኮ በትግሉ ወቅት ቢያንስ ያበሉትንና ያጠጡትን ወጭ ተለጣፊ ሹማምንት እንዲከፍሏቸዉ በህግ ሊጠይቁ ይችሉ ነበር!

ህሊናዉን ለሸጠ፤ እዉነትና ሃሰት በራሱ ዉስጥ መሟገታቸዉ ቢቀር፤ የተበደለ ህዝብ ብሶት ያለማቋረጥ ይሞግተዋል። በዚህ ምክንያት የህሊና እረፍት ፈጽሞ አያገኝም። ዉጫዊ ምቾቶች የህሊናን ቁስል አይሸፍኑም።

# 11 በመቶ አመታዊ እድገትና አርባ ጸጓሮች

የምእራብ ሀገሮች በተለይም የአለም ባንክና ተመሣሳይ ገንዘብ ነክ ድርጅቶች፤ የወያኔ/ኢህአዴግ ኢትዮጵያ ያደገችና የተመነደገች አገር እንደሆነች አሃዝን እንደ አቧራ እያስነሱ መበተናቸዉ የአደባባይ ምስጢር ነዉ። ለምሳሌ ደጋግመዉ ከሚረጯቸዉ አንዳንድ አሃዞች ከፊሎችን ብንመለከት፡

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ተማሪዎች ብዛት በአዉሮጳዉያን አቆጣጠር **1994** አ.ም. **26** ከመቶ ሲሆን፤ በ **2012** ደግሞ ወደ **86** በመቶ አድጓል።

ከ**$1.25** በቀን በላይ ገቢያቸዉ የሆኑ ሰዎች በ **1995** አ.ም. **37** ከመቶ ሲሆኑ በ **2012** ደግሞ ቁጥራቸዉ ወደ **63** በመቶ አድጓል።

በ እርሻ ላይ የሚዉል የገንዘብ ፈሰስ በአፍሪካ **4** ከመቶ ብቻ ሲሆን፤ በ ኢትዮጵያ ግን **21** ከመቶ ነዉ።

ሬዲዮ ያላቸዉ ሰዎች በ ኢትዮጵያ በ **1994 7** ከመቶ ብቻ ሲሆኑ በ **2005** ደግሞ ቁጥራቸዉ ወደ **49** ከመቶ ጨምሯል።

እነዚህን አሃዞች ሙሉ በሙሉ እንደቀረቡት መቀበል ቢያዳግትም (ለምሳሌ እንደ አርባ ጸጓር ኗሪዎች አይነት መናጢ ደሃዎች ኑሮ ጋር ቁጥሮቹ ስለሚጋጩ)፤ በሌላ በኩል ምንም አይነት እዉነትነት በደፈናዉ የላቸዉም ማለት አይቻልም። ለምሳሌ የተማሪዎች ቁጥርና የትምህርት ቤት ብዛቶች ቁጥር ወደ እዉነቱ የተጠጋ ቁጥር ይመስላል። ሆኖም እነዚህ ት/ቤቶች የሚፈለፍሏቸዉን ተመራቂዎች ችሎታና ለቦታ ብቁነት ብንመዝን ትምህርት በዘመነ ወያኔ እንዴት ደረጃዋ እንደወደቀ እንገነዘባለን።

በቅርቡ አንድ የመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ረዳት የፖለቲካል ሳይንስ ፕሮፌሰር በእንግሊዝኛ ስለ ህወሃት **12**ኛ ጉባኤ የጻፈዉን ስንመለከት፤ እሱዉ ደንቁሮ ተማሪዎችንም እንደሚያደነቁር መገንዘብ አይከብድም።

በርግጥ በወያኔ ደጋፊዎች በኩል "ልማትና እድገታችን መቶ በመቶ ነዉ አላልንም። እንደዚያም የለማና የበቃ አገር የለም። እንደ አርባ ጸጓር አይነቶቹ መቶ ለመሙላት በጎደሉን አሃዞች የሚወከሉ ናቸዉ" ብለዉ ሊከራከሩ ይችላሉ። ሆኖም የአለም ባንክ በ **2014** ባወጣዉ ዘገባ እንዲህ ይላል፤

**"Health extension agents are present in ALL kebeles and ensure that a basic range of health services are readily available to all families". (ገጽ 77)**

አርባ ጸጓር ከሄዱት ባለስልጣኖችም አንዱ ይህንን አዉስቷል። "ጤና ጣቢያዉን በሚመለከት ጤና ኬላና ጤና ኤክስቴንሽን ቀበሌዉ አለዉ። ሆኖም ግን የመጀመሪያ ርዳታ ብቻ ነዉ የሚሰጡት።"

ጤና ኬላና ኤክስቴንሽን አለም ባንክና ባለስልጣኑ እንደሚሉት አርባ ጸጓር ዉስጥ መኖሩ አጠራጣሪ ነዉ። አለዚያ አርባ ጸጓር ዉስጥ የመጀመሪያ ርዳታ የሚያገኙ ቢሆን ኖሮ አርሶ አደሮቹ "ሌላዉ ቢቀር እባብ የምትከላከል ጤና ጣቢያ እንኳን ስሩልን" አይሉም ነበር።

እንግዲህ እንዲህ ያለዉን አሃዝና ልማት ነዉ ከአርባ ጸጓር ኗሪዎች ሁኔታ ጋር ማነጻጸር ያለብን። እባብ ነድፏት የመጀመሪያ እርዳታ ሳታገኝ ህይወቷ ስላለፈዉ ወጣት ኗሪዎች እየተንገበገቡ እየተናገሩ፤ ቁሻሻ ወሃና የከብት ሽንት እየጠጣን ነዉ እያሉ፤ የአለም ባንክ ጠበብቶች አይናቸዉን በጨዉ ታጥበዉ "የህክምና አገልግሎት ለሁሉም ቤተሰብ ኢትዮጵያዊ ዉስጥ ይዳረሳል" ይሉናል።

ህክምና እንኳን ባለባቸዉ ቦታዎች የሚከፈል ገንዘብ ስላለዉና ይህም ካብዛኛዉ ህዝብ አቅም ዉጭ በመሆኑ ተጠቃሚዎቹ ባመዛኙ ገንዘብ እንደልብ ያላቸዉ ብቻ ሆነዋል። ታዲያ እንዲህ ከሃቅ የራቁ አሃዞች እያየንና እየሰማን ወያኔ/ኢህአደግ ስለሚያወራዉ የ **11** በመቶ እድገት መጠራጠር ይነስ**?**

## ያንድ አገር እድገት መለኪያ መመዘኛዎች መለወጥ አለባቸዉ

በ **21**ኛዉ ክፍለዘመን አንድ ሰዉ፤ በሰዉነቱ ታዉቆ ሙሉ ህይወት እየኖረ ነዉ ለማለት የሚያስፈልጉትን ቁሳቁስና መንፈሳዊ ፍላጎቶችን ሊያረካ ሲችል ነዉ። ምንድን ናቸዉ እነዚህ ፍላጎቶች**?**

ዋና ዋናዎቹ፡ ለራሱና ለቤተሰቡ በቂና የተመጣጠነ ምግብ ማግኘት፤ ንጹህና በቂ ወሃ ለመጠጥና ለሌሎች ጥቅሞች ሲያገኝ፤ ትምህርትና የጤና አገልግሎት ሲያገኝ፤ በደሃና በሃብታም መካከል ያለዉ ልዩነት እየጠበበ የሚሄድ ሲሆንና ጣራ የነካ ሳይሆን ሲቀር፤ የመናገር የመጻፍና የመደራጀት መብቱ ሲከበር፤ የህግ የበላይነት ሲኖርና መንግስት በፈለገዉና እንዳሻዉ የማያንገላታዉ ሲሆን፤ የሚመራዉን መንግስት በፈቃዱ መምረጥና ማቋቋም ሲችል፤ ወዘተ ናቸዉ። የአንድ ሀገር እድገት አሃዝ የሚሰጠዉ እነዚህን ሁሉ ግንዛቤ ዉስጥ ባስገባ መንገድ ሊሆን ይገባል። አንዳንድ ድርጅቶችም ይህንን የሰዉ እድገት ኢንዴክስ እያሉ ይጠቀሙበታል።

እዉነተኛዉን ያንድ አገር ገጽታ የሚያሳ ይህ ነው ።

ወደ ኢትዮጵያ ስንመጣም፤ የሚቀርበዉ አሃዝ የአላሙዲንን የመሰለ ባለሃብት ምቾትና አርባ ጸጓር የሚኖሩትን የደሃዋን የወ/ሮ ክቤ ዳዊትን ኑሮ ባማካይ የሚያቀርብልን ይሆናል። ያኔ **11** ከመቶ የሚባለዉ እድገት የዉሸት አሃዝና በትክክል ያልተሰራ ስሌት መሆኑን እንገነዘባለን። ምን አልባትም እዉነተኛዉ የ **"**እድገት**"** አሃዝ **"0"** ወይም አሉታዊ ቁጥር ሊሆን የሚችልበትም ሁኔታ ሊኖር ይችላል።

እስከዚያ የአለም ባንክና የምእራብ መንግስታት አንድ ወገንዮሽ አሃዝ ብቻ በተደጋጋሚ በማሰራጨት፤ ሙሉ የአገራችንን ስእል እንዳናይ ማደንቆራቸዉን ይቀጥላሉ።።


ዋቢዎች

**1.** አሃዞቹ የተገኙት **"One Foot on the Ground, One Foot in the Air: Ethiopia Delivery on an Ambitious Agenda (Develop Progress, September 2015)**

**2.** ስለ አለም ባንክ የተጠቀሰዉ **"World Bank Report 2014 Ethiopia, p.77**

**3.** የመቀሌ ዩኒቨርሲቲ መምህር ጽሁፍ **"Reflections on the 12th TPLF Congress", Assistant Professor of Political science and Strategic Studies, Mekelle University, Septemeber 2015**


ሰለሞን ገ/ስ

ኦክቶበር **2015**

、